የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 51
ADDIS ABABA - 30th June, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፩/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ማጽደቂያ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፯፻፹፭

## CONTENTS

Proclamation No. 121/1998
African Maritime Transport Charter Ratification
Proclamation ........................................ Page 785

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፩/፲፱፻፺

### የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተርን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተርን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የፈረመች በመሆኑ ፤

ቻርተሩ በቁርጥ ሥራ ላይ የሚውለው ፤ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገሮች የሁለት ሦስተኛው የማጽደቂያ ወይም ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ሰነዶች ለዋና ፀሐፊው ከደረሱ ከሰላሣኛው ቀን በኋላ እንደሚሆን ቻርተሩ ስለሚደነግግ ፤

ይህንኑ ቻርተር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአፍሪካ ማሪታይም ትርንስፖርት ቻርተር ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፩/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ቻርተሩ ስለመጽደቁ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሚኒስትሮች ምክር ቤት እ.ኤ.አ. በጁን ወር ፲፱፻፺፬ ቱኒዝ ላይ ባደረገው ስብሰባ የተቀበለው የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ጸድቋል ።

### PROCLAMATION No. 121/1998

### A PROLAMATION TO RATIFY AFTRICAN MARITIME TRANSPORT CHARTER

WHEREAS, Ethiopia had signed the African Maritime Transport Charter;

WHEREAS, it is stipulated in the Charter that the Charter finally enters into force thirty days after the Secretary - General of the OAU has received ratification, or similar, instruments of two-thirds of Member States;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democrtic Republic of Ethiopia has ratified said Charter at its session held on the 30th day of June, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Maritime Transport Charter Ratification Proclamation No. 121/1998."

2. *Ratification of the Charter*

The African Maritime Transport Charter, adopted by the Council of Ministers of the Organization of African Unity at its session held, in Tunis, in June 1994, is hereby ratified.

፫· <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሥልጣን</u>
የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ቻርተሩ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



3. *Power of the Minister of Transport and Communications*
The Minister of Transport and Communications is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Charter.

4. *Effective Date*
This Proclamation shall come into force as of the 30th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE